# በየካ ክፍለ ከተማ የ 6 ኛ ክፍል አንደኛ  መንፈቅ ዓመት የግብረገብ ትምህርት ሞዴል ፈተና 2017 ዓ.ም

**የተፈቀደው ጊዜ፡- 60 ደቂቃ**

**የጥያቄ ብዛት፡ 40**

**<u>አጠቃላይ ትዕዛዝ</u> !!**

ይህ የግብረብ ትምህርት ፈተና ነው። በዚህ ፈተና ውስጥ 40 ጥያቄዎች ተካተዋል፤

እያንዳንዱን ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሆነውን አማራጭ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልስ መስጫ በተሰጠው ወረቀት ላይ

በማጥቆር መልስ ይሰጣል።

በፈተና ላይ የተሰጡትን ትእዛዞች በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናውን መስራትይጠበቅባችኋል።

መልስ የሚሰጠው ከፈተናው ጋር በተያያዘው የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ ነው ፤በመልስ መስጫው ላይ ትክክለኛውን መልስ የሚጠቆረው በእርሳስ ብቻ ነው፤ትክክለኛውን መልስ በማጥቆር ሲሰራ በማጥቆር የተፈቀደው ቦታ ሙሉ በሙሉ በሚታይ መልኩ በደንብ መጥቆር አለበት፤የጠቆረውን መሌስ መቀየር ቢፈለግ በደንብ በማጥፋት መጽዳት አለበት።

ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተፈቀደው 60 ደቂቃ ነው፡፤ ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተሰጠው ሰዓት ሲያበቃ ለመስሪያነት የምንጠቀምበትን የመጻፊያ እርሳስ ማስቀመጥ እና ፈተናውን መስራት ማቆም አለብን። ፈተናው እንዴት እንደሚሰበሰብ በፈታኙ/ኟ እስከሚነገር ድረስ በቦታችን ተቀምጠን መጠበቅ አለብን ፤ መኮረጅ ወይም በፈተና ሰዓት የፈተናን ህግ የማያከብር ተፈታኝ ፈተናው አይያዝለትም፤ፈተናውንም እንዳይፈተን ይደረጋል። ፈተናውን መስራት ከመጀመራችሁ በፊት በመልስ መስጫው ላይ መሞላት የሚገባውን መረጃ ሁሉ በጥንቃቄ መሞላት አለበት።

***ፈተናውን መስራት ጀምሩ ሳይባል መጀመር አይፈቀድም !***

***<u>ትዕዛዝ አንድ፡ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡ አማራች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ የያዘዉን ፊደል በመምረጥ</u> የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ ፃፉ።***

1. ከሚከተሉት ውስጥ ስለ ኃላፊነት ትክክል *ያልሆነ* የቱ ነው ?

   ሀ) ጥሩ ምርጫ ማድረግ   ሐ ) ተጠያቂነት

   ለ) ታማኝ መሆን   መ) ለድርጊቶቻችን ተጠያቂነትን አለመውሰድ

2. ከሚከተሉት ውስጥ  የግል ኃላፊነት *ያልሆነው* የቱ ነው ?

   ሀ) እውነት መንገር   ሐ)  ንጽህናን መጠበቅ

   ለ) የክፍል ስራ መስራት   መ) ቤት መስራት

3. ……………..ማለት ድርጊቶችን ከውጤታቸው ጋር ማገናኘት ነው።

ሀ) ግልፅነት ለ) ማስተዋል ሐ) ግንኙነት መ) ተጠያቂነት

4. የግለሰብ ኃላፊነት ከ_________ ጋር የተያያዘ ነው።

ሀ) ግል ባህሪ ለ) ሐገር ኢኮኖሚ ሐ) ገንዘብ መ) ንፅህና

5. የቤተሰብ እና የማህበረሰብ ሃላፊነት ውስጥ **የማይካተተው** የቱ ነው ?

ሀ) እርስበርስ መከባበር ሐ) አርአያ መሆን

ለ) የቤተሰብ ኃላፊነትን መወጣት መ) በጓደኛ አለመቅናት

6. ግብርን በወቅቱ መክፈል እና ህግና ደንብን ማክብር የ.............. ኃላፊነት አይነቶች ናቸው።

ሀ) ቤተሰብ ለ) ሐገራዊ ሐ) ግል መ) ግል እና ቤተሰብ

7. ስለ ጠንካራ የስራ ባህልን ስንመለከት የምናነሳቸው ሁለት ወሳኝ ሀሳቦችን እነማን ናቸው?

ሀ) ባህልና ታታሪነት ለ) ገንዘብና መንግስት ሐ) ስራና ስራ መ) ታሪክና ወግ

8. _________ ማለት ጊዜና ጉልበትን ለአንድ የተወሰነ ስራ ወይም ተግባር በመደበኛነት ማዋልማለት ነው።

ሀ) ታሪክ ለ) ጠንክሮ መሥራት ሐ) ባህል መ) ታማኝነት

9. በኢትዮጵያ ውስጥ **የማይገኝ** ቅርስ የቱ ነው ?

ሀ) የአክሱም ሀውልት ሐ) የኮንሶ እርከን

ለ) የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስትያናት መ) የጎንደር ግንድ

10. " ተማሪ አሜን በጥናቱ እና በትጋቱ ሁልግዜም አንደኛ በመውጣት ለሁሉም አርአያ ነው " የአሜን ተግባር የማን ባሕርይ ነው?

ሀ) የታታሪ ተማሪ ለ) የሰራተኛ ሐ) የ ጥበበኛ መሪ መ) የተናጋሪ

11._______ ማለት በአንባቢውእናበሚነበበው ፅሁፍ መካከል የሚካሄድ የተግባቦት ሂደት ሲሆን ውጤቱም መረዳት ይሆናል።

ሀ) ታታሪነት ለ) መግባባት ሐ) መፃፍ መ) ንባብ

12._________ በ አሰሳ ንባብ/Skimming/ ሊነበብ **አይችልም።**

ሀ) አርዕስት ለ) ንዑስ አርዕስት ሐ) የቴሌቪዥን መመሪያ መ) ሥዕላዊ መግለጫዎች

13.በደቂቃ እስከ 1,500 ቃላትን ለማንበብ የሚያስችለን የንባብ ስልት የቱ ነው?

ሀ) የዳሰሳ ንባብ ለ) የሀረግ ንባብ ሐ) የአሰሳ ንባብ መ) ከሌሎች ጋርማንበብ

14. _________ ማለት ትክክለኛና ምክንያታዊ ውሳኔ ወይም ምርጫ የማቅረብ ችሎታ ነው።

ሀ) ግብረገብ ለ) ሀቀኝነት ሐ) ግልፅነት መ) ተማኝነት

15.''ተማሪ መንበረ ዜናዎችን ከታማኝ ምንጮች በመጠየቅ፣ መምህራኖቿን በመጠየቅ እና በማስተዋል ውሳኔዎችን ትወስናለች" የ ተማሪ መንበረ ድርጊት ምንን ያመለክታል ?

ሀ) ምሉዕነትን ሐ) ታማኝነትን

ለ) ግብረገባዊ ውሳኔን መ) ምስጢረኝነትን

16. ችግሮችን የመለየት ሂደት እና ተጓዳኝ የመፍትሄ ዘዴዎችን የመመልከት ሂደት _________ ይባላል።

ሀ) ወሳኔ ሰጪነት ለ) አሳቢነት ሐ) ተግባቢነት መ) ምክንያታዊነት

17.ጥሩ ውሳኔ ለመወሰን መከተል ***የማይገባን*** የቱን ነው?

ሀ) ችግሩን መለየት ለ) አማራጮችን አለማየት ሐ) መወሰን መ) መከታተል

18. _________ የውሳኔ አሰጣጥ ችሎታ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ሊሆኑ ከሚችሉ አማራጮች መካከል የመምረጥ ክህሎት ነዉ።

ሀ) ምክንያታዊነት ለ) ተጠያቂነት ሐ) አሳቢነት መ) ቆራጥነት

19.የግብረገባዊ ውሳኔ ተግዳሮት ***ያልሆነው*** የቱ ነው?

ሀ) በወላጆች የሚሰጥ ምክር ለ) የግንኙነት ግጭት ሐ) የበዛ ቁርጠኝነት መ) የአቻ-ግፊት

20.በግለሰብ(በግለሰቦች) ስብዕና እና በመካከላቸዉ ባለ ግንኙነት ላይ የተመሰረተ ግጭት_________ ይባላል ።

ሀ) ተጨማሪ ግጭት ለ) መተባበር ሐ) የማሕብረሰብ ግጭት መ) የግንኙነት ግጭት

21. በድርጊቶች መካከል ኢ-ተለዋዋጭ አቋምን የማሳየት ብቃት _________ ን ይወክላል።

ሀ) ተጠያቂነት ለ) ተለዋዋጭነት ሐ) ግብረገብ መ) ምሉዕነት

22. ______ ማለት አንድ ሰው ትክክል ነው ብሎ የሚያምንበትን ነገር እንዲተገብር የሚያደርግ ውስጣዊ ችሎታ ነው።

ሀ) ግልፅነት ለ) ድፍረት ሐ) ሃቀኝነት መ) ተለዋዋጭነት

23._______ እራስን በሌሎች ሰዎች ቦታ ላይ አስቀምጦ በማሰብ ስሜታቸውን መረዳት።

ሀ) ወጥነት ለ) ስለሌሎች ማሰብ ሐ) ኢ- ተለዋዋጭነት መ) ሃቀኝነት

24. _______የአንድን ሰው ችግር የመፍታት ብቃት ለማሳደግ እጅግ ጠቃሚ ግብዓት ነው።

ሀ) ገንዘብ ለ) መገንዘብ ሐ) ምሉዕነት መ) ማገንዘብ

25.እውነተኛ የግብረ ገብ ምሉዕነት የተላበሰ ሰው ባህርይ የሆነው የቱ ነው?

ሀ) መናቅ ለ) ኣላዋቂነት ሐ) ተለዋዋጭነት መ) በአቋም መጽናት

26. የግብረ ገብ ምሉዕነት አለመኖር ከሚያስከትለው ችግር ውስጥ ***የማይከተተው*** የቱ ነው?

ሀ) ስርቆት ለ) ሕገወጥነትን ማጋለጥ ሐ) ሙስና መ) ታማኝ አለመሆን

27. _______ በአንድ ሃገር ዉስጥ ያለ ማንኛዉም ሰው ሊከተላቸው የሚገቡ የስነ-ምግባር መርሆች ናቸው።

ሀ) ህጎች ለ) መገበያያች ሐ) መንገዶች መ ) መርሆች

28. ዜጎች የሃገሪቱን ህግ ለማክበር ያላቸው ዝግጁነትና ቁርጠኝነት የሚያሳየን የቱ ነው?

ሀ) ወጥነት ለ) ለህግ ተገዥነት ሐ) ታማኝነት መ) ህገ መንግስት

29. የህግ ተገዥነት አስፈላጊነት ***ያልሆነው*** የቱ ነው?

ሀ) ነፃነትን ለማግኘት ለ) ሰላምን ለመጠበቅ

ሐ) ለፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል መ) ሉዓላዊነትን ለመንጠቅ

30. ከሚከተሉት ውስጥ ስለ ህግ ትክክል የሆነው የቱ ነው ?

ሀ) ለሁሉም ዜጎች አያገለግልም ሐ) የህዝቦች ይሁንታ መገለጫዎች ናቸው

ለ) ለባለስልጣናት ብቻ ያገለግላል መ) ህግን አለማወቅ ተጠያቂ አያደርግም

31._______ የማህበረሰብ ለዉጥ ዘዴዎች ናቸው።

ሀ) ህጎች ለ) ህንፃዎች ሐ) መንግስታት መ) ሙስናዎች

32. የሙስና መገለጫ ***ያልሆነው*** የቱ ነው?

ሀ) ጉቦ መስጠት ለ) ዝምድና ሐ) ማጭበርበር መ) ወገንተኝነት

33. _______ ማለት ት ሐገርን የመምራት ሙሉ ስልጣን ማለት ነው።

ሀ) ህገ መንግስት ለ) ቁርጠኝነት ሐ) ሉዓላዊነት መ) የበላይነት

34.የመልካም ባህሪ ምሳሌ ***ያልሆነው*** የቱ ነው።

ሀ) ትሁት መሆን ሐ) ጥሩ ጓደኞችን ማምለጥ

ለ) ትክክል ለሆነው ነገር መወገን መ) ለሰሩት ስህተት ይቅርታን መጠየቅ

35._______ ማለት እምነት የሚጣልበት፤ ድርጊቶችን እና ውሳኔያችን በእምነት መምራት መቻል ማለት ነው።

ሀ) ምሉዕነት ለ) ታማኝነት ሐ) ራስን መቆጣጠር መ) ተጠያቂነት

36. የሀቀኛ ሰዎች መለያ ባህርይ ***ያልሆነው*** የቱ ነው?

ሀ) ስህተትን መቀበል ለ) እውነትን መናገር ሐ) ቃልን ማክበር መ) ማጋነን

37.የ _______ መኖር በአግባቡ በስነ-ምግባር ተኮትኩቶ ማደግን ያመለክታል።

ሀ) ሕግ ለ) መልካም ባህሪ ሐ) ዘመድ መ) ትምህርት

38.የአንድ ሰው ሀሳቡን፣ስሜቱን፣ምኞቱን፣ፍላጎቱንና ልምዶችን የመግታት ብቃት _______ነው።

ሀ) ራስን መቆጣጠር ለ) ጓደኝነት ሐ) ለሌሎች መከፈል መ) ቅንነት

39. ከሚከተሉት ውስጥ ስለ ህግ ተገዥነት አስፈላጊነትን ትክክል ***ያልሆነ*** የቱ ነው።

ሀ) ሰዎችን ከጉዳት ይከላከላል ሐ) የህዝቦችን መልካም ፈቃድ ያንፀባርቃል

ለ) አጠቃላይ ደህንነታችንን ያስጠብቅልናል መ) በህዝቦች መካከል መተማመንን ይሸረሽራል

40. መልካም ባህሪ አለመላበስ ከሚያስትላቸው ውጤቶች ውስጥ ***የማይከተተው*** የቱ ነው?

ሀ) መዋሸት ለ) ስርቆት ሐ) የተገባ አለባበስ መ) የፈተና ኩረጃ